በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**የሰ/መ/ቁ.** 237535

ህዳር 27 ቀን 2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻዉ አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሰናይት አድነዉ

**አመልካቾች፡-**

1. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቴክ/ሙያ ትምህርት ስ/ሳ/ቴክኖሎጂ ቢሮ    ዐቃቢ ህግ መርማሪ
2. የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ባለስልጣን    ኮሽ ቀረቡ

**ተጠሪ-** ባህረይ ታደሰ ----- ጠበቃ ማንጉዳይ ወንድሙ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የግንባታ ዉልን የሚመለከት ነዉ፡፡ ክርክሩ የተጀመረዉ በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ የቦርቻ ወረዳ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ፕሮጀክት ለመገንባት ከ1ኛ ተከሳሽ (የደቡብ ብ/ብ/ሕ/መንግስት ቴክንክና ሙያ ትም/ስልጠና ቢሮ) ጋር በ2007 ዓ.ም ዉል አድርገናል፡፡ የግንባታ ቦታዉ ተስተካክሎ ለግንባታ ሙሉ በሙሉ ምቹ እስከሚሆን ድረስ 430 ቀን ስጠብቅ ቆይቻለሁ፡፡ እንዲህም ሆኖ ስራዉን ስሰራ ቆይቻለሁ፤ ነገር ግን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልግ መሆኑን ጠቅሼ መጋቢት 08 ቀን 2007 ዓ.ም የፃፍኩለትን ደብዳቤ ተከትሎ አሠሪዉ መስሪያ ቤት እስከ ግንቦት 30 ቀን 2012 ዓ.ም አራዝሞልኛል፡፡ በግንባታዉ ሂደት የግንባታ ቁሳቁሶች ዋጋ መጨመር እና የዉጭ ምንዛሪ ዋጋ በመዉረዱ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግልኝ ባቀረብኩለት ጥያቄ መሠረት የስር 1ኛ ተከሳሽ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ ተዘጋጅቶ ሳለ የሲዳማ ህዝብ ክልል መንግስት በመደራጀቱ በአዲሱ ክልል የዋጋ ማስተካከያ እንዲፈጸም መስከረም 08 ቀን 2013 ዓ.ም ደብዳቤ ተጽፎላቸዋል፡፡ የቀድሞዉ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መስሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ከነዉሉ የተላለፈለት 1ኛ አመልካች (የስር 2ኛ ተከሳሽ) የተሻሻለ ዉል እንዲያቀርብ ለ2ኛ አመልካች ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም ደብዳቤ የፃፈ ቢሆንም፣ 2ኛ አመልካች ይህን ለመፈጸም ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ ስራዉን መጨረስ እንዲችል ማስጠንቀቂያ ስሰጥ የቆየሁ ቢሆንም አልተፈጸመልኝም፡፡ የስር 1ኛ ተከሳሽ የገባዉን ዉል 1ኛ አመልካች የመፈጸም ግዴታ የተላለፈ ከመሆኑ አኳያ የስር 1ኛ ተከሳሽ የተቀበለዉ የዋጋ ማስተካከያ በዉሉ አንቀጽ 62 መሠረት የዉሉ አካል በመሆኑ በፍርድ ኃይል እንዲፈጽሙ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካቾች የመጀመሪያ መቃወሚያ በማስቀደም በጋራ በሰጡት መልስ፣ በዉሉ አንቀጽ 62 መሠረት የዋጋ ማስተካከያዉ የህግ ድጋፍ የለዉም፤ ግንባታዉ ያልተጠናቀቀዉ በተጠሪ የአቅም ማነስ እና ሠራተኞችንና የግንባታ ዕቃዎችን ባለማቅረቡ ምክንያት ነዉ፡፡ ግንባታዉ ያልተጠናቀቀዉ በዚህ ምክንያት ስለመሆኑም ጳጉሜ 13 ቀን 2010 ዓ.ም በፃፈዉ ደብዳቤ ተጠሪ ይቅርታ ጠይቋል፡፡ በጠቅላላ የዉል ሁኔታዎች አንቀጽ 62.1 ላይ በተደነገገዉ መሠረት የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገዉ ከ 18 ወር በላይ ጊዜ ለሚጠይቅ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ፕሮጀክት ከ18 ወር በታች ጊዜ የተሰጠዉ በመሆኑ የዋጋ ማስተካከያ ሊጠየቅበት አይገባም፡፡ የዉል ማጠናቀቂያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ የማራዘሚያ ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ ሐምሌ 2008 ዓ.ም ሲሆን፣ ተጠሪ የማራዘሚያ ጊዜ የጠየቁት ግንቦት 05 ቀን 2012 ዓ.ም ነዉ፡፡ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገዉ ተሰርቶ ላለቀ እና ዋጋ ላልተከፈለበት ስራ ብቻ ነዉ፡፡ ተጠሪ ያቀረበዉ የዋጋ ማስተካከያ ተሰርቶ ክፍያ ለተፈጸመበት ስራ በመሆኑ ተቀባይነት የለዉም፡፡ በ2012 ዓ.ም የወጣዉ የግዥ መመሪያ ቁጥር 001/2012 አንቀጽ 16.14.2(ሀ) ላይ በተመለከተዉ መሠረት የዋጋ ማስተካከያ የሚጠየቀዉ በዉሉ የጊዜ ማዕቀፍ ዉስጥ ለተሰራ ስራ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ከዚህ መመሪያ ጋርም የሚጋጭ ነዉ፡፡ በዉሉ አጠቃላይ ክፍል እና ልዩ ክፍል ተጠቅሰዉ ላልተቀመጡ እቃዎች ዋጋ ማካካስ አይቻልም፡፡ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገዉ ከማዕከላዊ እስታትክስ ኤጀንሲ ወይም ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የመጣ የዋጋ ኢንዴክስ የዋጋ ማሳያ አመላካች ካለ ብቻ ነዉ፡፡ ተጠሪ የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ማቅረቡ ከGCC እና SCC እንዲሁም ከክልሉ አዋጅ ቁጥር 146/2012 እና የአፈፃፀም መመሪያ ማኑዋል መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ ዉድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ፕሮጀክቱ በሲዳማ ክልል ዉስጥ የሚገኝ በመሆኑ እና ባለቤትነት መብቱም በዚህ አግባብ ተላልፏል የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ በማቅረቡ ከክርክሩ ዉጪ ሆኗል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኝ በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የዉል ጠቅላላ ክፍል አንቀጽ 62.1 የግንባታ ጊዜ ከ18 ወራት በላይ የሚወስድ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ግንባታ ከጀመረ አንስቶ 12 ወራት በኋላ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ እንደሚፈቀድ ይደነግጋል፡፡ በግራ ቀኝ ዉል መሠረት ስራዉ የሚጠናቀቀዉ በ18 ወራት ጊዜ ዉስጥ ነዉ፡፡ የአሠሪዉ ጥፋት በሆኑ በተለያዩ ምክንያቶች 375 ቀናት ያለስራ ባክነዋል፡፡ በዚህም የዉሉ ጊዜ እስከ መጋቢት 08 ቀን 2007 ዓ.ም ተራዝሟል፡፡ በዉሉ አጠቃላይ ሁኔታ ቁጥር 62.6(ለ) መሠረት በዉል የተመለከተዉ ጊዜ ካለፈ ወይም ማራዘሚያ ከተሰጠ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በተጠሪ የቀረበዉ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ፡፡ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄዉ ተቀባይነት ያገኘዉ ተዋዋይ በሆነዉ መስሪያ ቤትና በዚህ ዙሪያ ህግ የሚያወጡ የኮንስትራክሽን ባለ ስልጣን እንዲሁም ሂደቱን የሚቆጣጠሩት የደቡብ ግንባታ ቁጥጥር ድርጅት አምነዉ ባደረጉት የጽሑፍ ልዉዉጥ መሠረት ነዉ፡፡ በመሆኑም አሠሪ አካላት ተስማምተዉ በጽሁፍ አድርገዉ ያለፉትን አመልካቾች ወደ ኋላ ሊመልሱ አይችሉም፡፡ የዉል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አፈፃፀም ጊዜ እየተራዘመ በሄደ ቁጥር የግንባታ ዕቃዎች ይጨምራሉ፤ በዉል ጠቅላላ ሁኔታ ቁጥር 62.3፣ 62.6 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም ይህንኑ ታሳቢ ያደረጉ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ተቀባይነት ያለዉ ነዉ፡፡ የዉሉ ልዩ ክፍል በዉሉ በዝርዝር ያልተመለከቱ የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ለዋጋ ማስተካከያ አይቀርብባቸዉም የሚል ድንጋጌ የለዉም፡፡ የግንባታ ግብዓት ዕቃዎች ዋጋ ግምት ከፌዴራል ማዕከላዊ እስታትክስም ይሁን የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ከገለልተኛ ተቋማት ተጣርቶ የማሻሻያ ጥያቄ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በመሆኑም በዉል ጠቅላላ ሁኔታዎች አንቀጽ 62 መሠረት ዉሉ ከመጀመሩ በፊት ስራ ላይ ሳይዉል ቆይተዉ የባከኑ 375 ቀናት በኋላ የዉሉ ጊዜ ከጀመረ ጀምሮ በሚቆጠረዉ መሰረት ለተሰራ ስራ ዉላቸዉ ዉስጥ ያለ ግንባታ ግብአቶች ላይ የፌዴራል ፕላን ኮሚሽን፣ ከማዕከላዊ እስታቲክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ ወይም በሚተኩበት ስልት እንደገና ተጣርቶ በሚመጣ የዋጋ ኢንዴክስ ላይ ባለዉ የሂሳብ አሰራር መሠረት የዋጋ ማስተካከያ አመልካቾች ለተጠሪ ይፈጽሙ በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉም በዚሁ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ሲሆን፣ አመልካቾች ህዳር 19 ቀን 2015 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በቀረበ የሰበር አቤቱታ በሀዋሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚሉባቸዉን ምክንያቶች በመዘርዘር ታርሞ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ በአጣሪ ችሎት ተመርምሮም የዋጋ ኢንዴክስ ከማዕከላዊ እስታቲክስ ኤጀንሲ ተጣርቶ ቀርቦ በፍርድ ቤት የቀረበዉ ጉዳይ ተለይቶ ታዉቆ ዳኝነት ሳይከፈልበት እና ዉጤቱ ሳይታወቅ አመልካቾች ክፍያ እንዲከፍሉ የወሰኑበትን አግባብ ግራ ቀኝ በተገኙበት አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ያስቀርባል ተብሏል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪ ታህስ 18 ቀን 2015 ዓ.ም አዘጋጅተዉ በጠበቃዉ በኩል ባቀረቡት መልስ በክልሉ በየደረጃዉ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት ጸንቶ ይወሰንላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የሰበር አቤቱታቸዉን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ከስር ጀምሮ የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኝ ክርክር ይዘት አጠር አጠር ባለ መልኩ ሲታይ ከፍ ሲል የተመለከተዉን ሲመስል፣ ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረዉም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለጠየቁት ዳኝነት መሠረት ያደረጉት፣ ከስር 1ኛ ተከሳሽ ጋር ተደርጎ የሲዳማ ክልል መቋቋሙን ተከትሎ መብትና ግዴታዉ ወደ አመልካቾች በተላለፈዉ ዉል መሠረት የግንባታ ስራዉን ሲያከናዉን ቆይቶ በኋላ ላይ በተከሰተ የዋጋ ጭማሪ እና መለዋወጥ ምክንያት የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ በተጠሪ የቀረበዉን ጥያቄ የስር 1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ የነበረ ቢሆንም አመልካቾች በዋጋ ማስተካከያዉ መሠረት የሚጠበቅባቸዉን ግዴታ ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም የሚል ነዉ፡፡ የተጠየቀዉ ዳኝነትም አመልካቾች ይህንኑ በፍርድ ኃይል እንዲፈጽሙ የሚል ነዉ፡፡ አመልካቾች በበኩላቸዉ ተጠሪ የዋጋ ማስተካከያ የመጠየቅ መብት የላቸዉም የሚል እና ሌሎችንም መከራከሪያዎች በማንሳት የተጠሪ ዳኝነት ዉድቅ ይደረግላቸዉ ዘንድ ተከራክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኝን ካከራከረ በኋላ የሰጠዉን ዳኝነትም *"በዉላቸዉ አንቀጽ 62 መሠረት ዉሉ ከመጀመሩ በፊት ስራ ላይ ሳይዉል ቆይቶ የባከኑ 375 ቀናት በኋላ በዉሉ መሠረት ስራ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠረዉ መሠረት ለተሰራ ስራ በዉላቸዉ ላይ*

*በተመለከቱት የግንባታ ግብአቶች ላይ የፌዴራል ፕላን ኮሚሽን፣ ከማዕከላዊ እስታትክስ ኤጀንሲ የዋጋ እንዴክስ እንደገና ተጣርቶ በሚመጣ የዋጋ ኢንዴክስና በዉሉ ላይ ባለዉ የሂሳብ አሠራር መሠረት የዋጋ ማሻሻያ አመልካቾች ለተጠሪ ይፈጸሙ"* የሚል ስለመሆኑ የዉሳኔዉ ይዘት ያሳያል፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህን ዉሳኔ የወሰነዉም የተጠሪ ዳኝነትም ይሄዉ በመሆኑ ምክንያት ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ የፍርድ ቤቱ ዉሳኔ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ የተያዘዉን ጭብጥ ከመመርመራችን በፊት፣ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ግልጽ እና ለፍትሐዊ ዉሳኔ አሰጣጥ የሚያመች መሆን አለመሆኑን አስቀድሞ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀዉ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸዉን የጽሑፍ ክርክር መርምረዉ፣ በቃል የሚቀርቡ ክርክሮችን አዳምጠዉ፣ ማስረጃዎችን መዝነዉ እና መሠረታዊ ህጎችን ተርጉመዉ ዉጤት ላይ መድረስ ይችሉ ዘንድ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፡፡ የሥነ ሥርዓት ደንቦች ዋና ዓላማ ተከራካሪዎች በሕግ/በዉል በተሰጧቸዉ መብቶቻቸዉና ጥቅሞቻቸዉ መሠረት ፍትሕ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ የፍርድ ቤቶችን ተግባርና ሥርዓት መልክ ለማስያዝ ነዉ፡፡ እነዚህ ደንቦች የተቀየሱት የዳኝነት ስራ በተመቻቸና በቀለጠፈ ሁኔታ እንዲከናወንና ሙግት ፍፃሜ እንዲያገኝ ነዉ፡፡  ይህን ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ የተለያዩ ደንቦች እና መርሆዎችን ይደነግጋል፡፡ የክስና የመከላከያ መልስ ማመልከቻዎች ምን ምን ሁኔታዎችን አሟልቶ መቅረብ እንዳለባቸዉ፣ ክሱን የሚያየዉ ፍርድ ቤት ክርክሩን እንዴት እንደሚመራዉ፣ ደረጃ በደረጃ ምን ዓይነት እርምጃዎች በመዉሰድ ከሕጉ አንፃር አግባብነት የሚኖራቸዉን አከራካሪ ነጥቦች በመለየት የተከራካሪ ወገኖችን መብትና ግዴታዎች እንዴት አንጥሮ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት የሚወሰነዉ በሥነ ሥርዓት ደንቦች ነዉ፡፡ በአጠቃላይ ክርክሮች በዘፈቀደ ሳይሆን ሥርዓት ባለዉ ሁኔታ እንዲመሩ ማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትን፣ ብሎም ክርክሮች ባነሰ ወጪ እና ጊዜ መቋጫ እንዲያገኙ በማድረግ የክርክሩ ሂደትም ሆነ ዉጤቱ ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ረገድ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ የተመለከቱት ደንቦች የሚኖራቸዉ ሚና ከፍተኛ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ ላይ የተመለከቱ ደንቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ተከራካሪ ወገኖች ያላቸዉ ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ክርክሮች በህጉ ላይ በተመለከቱት ደንቦች መሠረት ሥርዓት ባለዉ መልኩ እንዲመሩ ማድረግ እና ሂደቱንም የመቆጣጠር ዋነኛ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች መሆኑም እሙን ነዉ፡፡

በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጋችን ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ ደንቦች ዉስጥ አንዱ የክስ እና መልስ አቀራረብ ሥርዓትን የሚመለከተዉ ደንብ አንዱ ነዉ፡፡ የሥነ ሥርዓት ደንቦችን በመከተል የሚቀርቡ ማመልከቻዎች አግባብነት ያላቸዉንና ሊወሰኑ የሚገባቸዉን አከራካሪ ነጥቦች ግልጽ ስለሚያደርጉ የፍርድ ቤቱን ስራ ያቀላሉ፡፡ ፍርድ ቤት በሥነ ሥርዓት ደንቦች የተደነገገዉን በመከተል ክርክሩን በስልታዊ መንገድ ከመራዉ ትክክለኛ ፍትሕን በቀለጠፈ ሁኔታ ለመስጠት ያስችለዋል፡፡ ይህን ግምት ዉስጥ በማስገባትም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓታችን የክስ አቤቱታ አቀራረብን አስመልክቶ የተለያዩ ድንጋጌዎች አሉት፡፡ በዚህም መሠረት ከሳሽ የሚያቀርበዉ ክስ ለክሱ ምክንያት ናቸዉ የሚላቸዉን ፍሬ ነገሮችንና የተጠየቀዉን ዳንነት በግልጽ ሊያሳይ እንደሚገባ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 222 (1/ረ) እና 224 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ህጉ የከሳሽ ክስ በዚህ ሁኔታ እንዲቀርብ የፈለገበት ምክንያትም ተከሳሽ የከሳሽን ክስ ይዘት በአግባቡ ተረድቶ በበኩሉ አለኝ የሚለዉን መከራከሪያ ማቅረብ እንዲችል፣ ፍርድ ቤቱም ስለ ክርክሩ ሁኔታ በአግባቡ ተረድቶ ትክክለኛ ጭብጥ በመያዝ ክርክሩ በአግባቡ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መርቶ ፍትሐዊ ዉሳኔ ላይ እንዲደርስ ለማስቻል እንደሆነ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ ክሱን በዚህ ሁኔታ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን፣ ፍርድ ቤቱም፣ ሌሎች በህጉ ላይ የተመለከቱት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነዉ፣ የከሳሽ ክስ በርግጥም ከላይ በተጠቀሱት የህጉ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተዉን መስፈርት አሟልቶ የቀረበ መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ በህጉ የተመለከተዉ ድንጋጌ እንዳለ ሆኖ፣ ከሳሽ ያቀረበዉ ክስ ግድፈት ሊኖርበት የሚችል ሲሆን፣ ግድፈቱን ማቃናት ከሚቻልባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ የክስ አቤቱታዉ እንዲሻሻል በማድረግ ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ 91 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ከሳሽ ክሱ ግድፈት ያለበት መሆኑን ተረድቶ ፍርድ ቤቱን አስፈቅዶ አሻሽሎ ማቅረብ እንደሚችል፣ እንዲሁም ለፍትሐዊ ዉሳኔ አሰጣጥ ተገቢ ነዉ ብሎ ካመነ ከሳሽ የክስ አቤቱታዉን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ማዘዝ የሚችል መሆኑን ይነግረናል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤት የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ ዉሳኔ ለመስጠት የሚቸገር መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ የማድረግ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በአንድ በኩል የስር 1ኛ ተከሳሽ ተቀብሎ የነበረዉን የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ የአሁን አመልካቾች ተቀብለዉ መፈጸም ባለመቻላቸዉ በፍርድ ኃይል ተገደዉ የዉሉ አካል እንዲያደርጉ የሚል ይዘት ያለዉ ይመስላል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የስር አንደኛ ተከሳሽ ተጠሪ የጠየቁትን የዋጋ ማስተካከያ ተቀብሎ የዉሉ አካል ሆኖ ነገር ግን አመልካቾች የዉሉ አካል በሆነዉ የዋጋ ማስተካከያ መሰረት ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚጠይቅ ይመስላል፡፡ የተጠሪ ክስ የስር ተከሳሽ የተቀበለዉን የዋጋ ማስተካከያ አመልካቾች ተቀብለዉ የዉሉ አካል እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ነዉ በሚል ደምድሞ እንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ዳኝነት የሚጠየቅበት አይደለም ተብሎ ክሱ እንዲሰረዝ መወሰን እንዳይቻል፣ ከላይ እንደተመለከተዉ፣ ተቀባይነት ባገኘዉ የዋጋ ማስተካከያ መሠረት አመልካቾች የሚጠበቅባቸዉን ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚል ይዘት ያለዉ ይመስላል፤ ዳኝነቱ በዋጋ ማስተካከያዉ መሠረት ክፍያ እንዲፈጸም የቀረበ ነዉ በሚል ደምድሞ በዚህ መሠረት አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት እንዳይቻል፣ ከዉሉ በኋላ በተከሰተ የዋጋ ንረት ምክንያት የዋጋ ለዉጥ የታየባቸዉ የግንባታ ዕቃዎች ዝርዝር፣ ዉሉ ሲደረግ በነበረዉ የእያንዳንዱ የግንባታ ግብአት (ዕቃ) ዋጋ ላይ የተጨመረዉ የገንዘብ መጠን፣ በተደረገዉ የዋጋ ማስተካከያ መሰረት አመልካቾች እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸዉ የገንዘብ መጠን እና መሰል ሁኔታዎችን በዝርዝር አያሳይም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ተጠሪ ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ እና ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ መስጠት የሚቻል አለመሆኑን ነዉ፡፡ በመሆኑም፣ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሳቸዉን አሻሽለዉ እንዲያቀርቡ ማድረግ ሲገባዉ፣ ይህን ባለማድረግ ግልጽ ባልሆነ ክስ ላይ ቆሞ ክርክሩን በመምራት የሰጠዉ ዉሳኔ መታረም ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ የሰጠዉ ዉሳኔ ሊፈጸም የሚችል ነዉ ወይ? ወደሚለዉ ጭብጥ እንመለስ፡፡ በመሠረቱ የዳኝነት ስራ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት ዕዉቅና የተሰጣቸዉን የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርሆዎችን ከግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ የሚታወቅ ነዉ (አንቀጽ 12 ይመለከቷል)፡፡ የፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጉ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ዕዉቅና ከሚሰጣቸዉ መርሆዎች ዉስጥ አንዱ የግልጽነት እና የተጠያቂነት መርህ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጋችን ላይ ከተመለከቱት የተለያዩ ድንጋጌዎች የምንገዘበዉ ነዉ፡፡ የፍርድ/ዉሳኔ አፃፃፍ እና ይዘቱን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ ከአንቀጽ 180-183 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎችም እነዚሁን መርሆዎች ታሳቢ በማድረግ የተቀረጹ ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የፍርድ አፃፃፍ ሥርዓት የዳኝነት ነፃነት እና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ተጠያቂነት መርህ ከሚረጋገጡባቸዉ መንገዶች ዉስጥ አንዱ ስለመሆኑም መገንዘቡ ተገቢ ነዉ፡፡ በፍርድ ዉሳኔ ላይ ስለሚሰፍሩ ነገሮች በሚል ርዕስ በፍትሐብሔር ሥ/ሥርዓት ህጋችን አንቀጽ 182(1) ላይ በተለይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለዉ፣ አንድ የፍርድ ዉሳኔ የተያዘዉን ጭብጥ፣ ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና የተወሰነበትን ምክንያት የያዘ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ የዳኝነት ሥራ የመጨረሻ ግቡ ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ መስጠት መሆኑ የሚታወቅ ነዉ፡፡ ግልጽ ዉሳኔ አለመስጠት፣ ዉሳኔዉ ለአፈፃፀም አስቸጋሪ እንዲሆን ወይም ሳይፈጸም እንዲቀር ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ፣ ለአፈፃፀም የቀረበዉ ዉሳኔ ይዘት ግልጽ ባለመሆኑ ወይም አከራካሪ መሆኑን ተከትሎ በትርጉም ክፍተቱን ለመሙላት በሚደረግ ጥረት በዋናዉ ፍርድ የተረጋገጠ መብትና ግዴታ በአፈፃፀም እንዲለወጥ ወይም እንዲሻሻል የማድረግ ዉጤት ሊያስከትል የሚችል ሲሆን፣ ይህ መሆኑም የፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ተገማችነት እና ተፈፃሚነት ጥያቄ ዉስጥ እንዲገባ ምክንያት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ሲሰጡ፣ የሚሰጡት ዉሳኔ ግልጽ እና ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 183 (1-መ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌም ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት ዉሳኔ ተከሳሽ ለከሳሽ የሚፈጽመዉን ግዴታ በግልጽ ማሳየት እንዳለባቸዉ የሚያስገድድ ነዉ፡፡ ከዚህ አንፃር የተያዘዉን ጉዳይ ስንመለከት፣ የሀዋሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት *"የፌዴራል ፕላን ኮሚሽን ከማዕከላዊ እስታትክስ ኤጀንሲ የዋጋ ኢንዴክስ እንደገና ተጣርቶ በሚመጣ የዋጋ ኢንዴክስና በዉሉ ላይ ባለዉ ሂሳብ አሠራር መሠረት የዋጋ ማሻሻያ አመልካቾች ለተጠሪ ያድርጉ"* በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ ያላለቀለት፣ በአፈፃፀም ወቅት ከግንባታ ዕቃዎች ግምት ጋር በተያያዘ ግራ ቀኝ አዲስ ክርክር እንዲያቀርቡ የሚጋብዝ በመሆኑ ሊፈጸም የሚችል ዉሳኔ ነዉ ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተዉ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክሳቸዉን አሻሽሎ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ ተሻሽሎ በግልጽ የቀረበዉን ክስ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኝን ክርክር ሰምቶ እና መርምሮ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ፣ በግልጽ ያልቀረበዉን የተጠሪን ክስ መሰረት በማድረግ ለአፈፃጸም አዳጋች የሚሆን ዉሳኔ መስጠቱ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህን ሳያርም የስር ፍርድ ቤቱን ዉሳኔ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 30192 ላይ ሚያዝያ 07 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የሲዳማ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 03372 ጥቅምት 04 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ተሸረዋል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዘግቶ የነበረዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ ክሳቸዉን አሻሽለዉ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ፣ ተሻሽሎ በቀረበዉ ክስ ላይ በመመስረት የግራ ቀኝን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተገቢ ነዉ የሚለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 211 (2) መሠረት ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. የሰበር አጣሪ ችሎት ህዳር 21 ቀን 2016 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !